# ዴሞክራሲያ

ዴሞክራሲያ ቅጽ.41 ቁጥር 8 ግንቦት-ሰኔ 2008 ዓ.ም

## <u>የት ደርሰናል? ምንስ አትርፈን ምንስ ማሻሻል አለብን፣ ለወደፊት?</u>

ማናቸውም ዓላማና ግብ ያለው እንቅስቃሴ በሂደቱ የተጓዘበትን ጎዳና በአንድ በተወሰነ ወቅት ላይ ጊዜ ወስዶ ወደ ኋላ መለስ ብሎ  መቃኘት ይኖርበታል። በዚህም የደረሰበትን፥ አብሮም እዚያ ለመድረስ ባረገው ጉዞው የወጣ የወረደበትን፣ ያጣውን ያገኘውን፣ ያጠፋውን ያለማውን፣ ጥንካሬውን ድክመቱን፣ የሚያስተውልበት ብቻ ሳይሆን ለእንግዲሁ የዓላማውን ግብ መሳካት ሊያፋጥኑ ይችላሉ የተባሉትን አስፈላጊና ወሳኝ ዝግጅቶችን ለመንደፍና ለማቀድ፤ ብሎም ለተፈፃሚነታቸው መወሰድ ያለባቸውን ማናቸውንም እርምጃዎች ለማቀናጀት እንዲያስችለውም ጭምር ነው። ይህ የስርዓት ለውጥ ኣንዲመጣ ለሚታገል ህዝባዊ እንቅስቃሴ ደግሞ አስፈላጊና የግድ መሆን ያለበት ብቻ ሳይሆን ወሳኝነትም ያለው ጉዳይ ነው።

ወደ ግማሽ ምዕተ ዓመት እያስቆጠረ ያለው የኢትዮጵያ ሕዝብ ትግል፥ ለዘመናት ቀይዶት የቆየውን በዝባዥና ጨቋኝ ሥርዓት ለአንዴም ለሁሌም ገርስሶ ጥሎ በምትኩ ስር ነቀል ለውጥ በአገሪቱ ለማምጣት ዳር እስከዳር ሆ ብሎ በአንድ ላይ ተንቀሳቅሷል። ለዘመናት ሳያሰልስ ያጎሳቆሰለውና በሁሉም መስክ ከሰውነት ውጭ አድርጎት የነበር አስከፊ ጨቋኝና በዝባዥ ሥርዓት ያስከተለው እንቅስቃሴ መሆኑ ግልጽ ነው። በመሆኑም፣ በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ እስከዚያን ወቅት ድረስ በአብዛኛው ሕዝብ አእምሮ ውስጥ ይደመሰሳል፥ ይገረሰሳል ተብሎ ይታመን ያልነበረውን፣ ሥርዓቱ የተጋመደበትን መዋቅር ከሥር መሠረቱ ነቅሎ ለመገርሰስ ያስገመገመ ስለነበር በእርግጥም ምድር አንቀጥቅጥ ነበርና በታሪካችን ደማቁን ሥፍራ ሊጎናፀፍ ይገባዋል ቢባል ተገቢ ነው ብለን እናስባለን።

ይህ በኢትዮጵያ አርሶ አደሮች፥ ላብ አደሮች፥ ተማሪዎች፥ መምህራን፥ ሴቶች፥ ጭቁን ወታደሮች፥ የመንግሥት ሠራተኞች፥ የክርስትናና የእሥልምና ሃይማኖት ተከታዮች ሌሎችም የሕብረተሰቡ ክፍሎች በአንድ ላይ ሆነው የተሳተፉበት ታላቅ ሕዝባዊ እንቅስቃሴ አይቀሬነቱ ይታሰብ የነበረ ቢሆንም፥ ድንገተኛነቱ ግን ሁሉንም ያስገረመ እንደነበር እሙን ነው። የዚህ እንቅስቃሴ ግብታዊነት በተገፋውና በተጨቆነው ህዝብ ልብ ውስጥ የጫረው ፍፁም የደስታ ስሜትና የሰነቀው የብሩህ ተስፋ እንዳለ ሆኖ፥ ግና ይህን ብሩህ ተስፋውን በአስተማማኝ ሁኔታ ለማስረገጥና እውን ለማድረግ አስፈላጊ የሆኑት የትግል መሳሪያዎቹ ማለትም ትግሉን አደራጆቹ፥ አቀናጆቹ፥ ቀስቃሶቹና እቅጣጫ ሰጪዎቹ ያልነበሩበት ወይም ቢኖሩም ገና በበቂ ተጠናክረው የተገኙበት ሁኔታ ስላልነበረ እንቅስቃሴው ከቶም የዋዛ እንዳልሆነ ያኔም በግምት ውስጥ ሳይገባ አልቀረም፤ ዛሬም ኢትዮጵያ ያለችበት ሁኔታ ይህንኑ (የተቀናጀ ኃይል አለመኖርን) የሚያረጋግጥ ሆኖ እናገኘዋለን።

በዚያ በ1966፣ ግና እኒህ የእንቅስቃሴው ጉድለቶች እንዳሉ ሆነውም የዘመናት በደልና ግፍ የወለደው የምሬት ውጤት በመሆኑ በትግሉ ሂደት ውስጥ ያልተሟሉትን እያሟላ መጠናከር ያለባቸውን እያጠናከረ መገሥገሱን ተያያዘው። በጊዜው አንስቷቸው የነበሩት ፖለቲካዊ፥ ኤኮኖሚያዊና ማህበረሰበዊ ጥያቄዎች ማለትም የጉልተኛው ሥርዓት የመሬት ሥሪት አከትሞ መሬት ለአራሹ እንዲሆን፤ ሠራተኛው በአሰሪው የሚደርስበትን መረን የለቀቀ ብዝበዛና ሌሎች መብቶቹን የሚያስከብርበት ማህበሩ ከአገዛዙ ቁጥጥር ነፃ እንዲሆን፤ብሔረሰቦች የራሳቸውን ዕድል በራሳቸው እንዲወስኑ፤ የሃይማኖትና የፆታ እኩልነት እንዲረጋገጥ፤ ...ወዘተ የሚሉቱ መልስ ያገኙ ዘንድ ታግሏል። ፍትህ ርትዕ የሰፈነበት፥ የህግ የበላይነት የተረጋገጠበት፥ ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች ተከብረው ሁሉም ዜጋ በእኩልነትና በአንድነት የሚኖርበት ሥርዓት እውን እንዲሆን ዓላማውና ግቡ አድርጎ የተጀመረ ሕዝባዊ እንቅስቃሴ በትግሉ ሂደት ውስጥ ከተለያዩ አቅጣጫዎች የሚደርሱበት ተፅኖዎች ይኖራሉ። በራሱ ከእንቅስቃሴው የወገን ጎራ የሚፈልቁ በጎም ሆኑ መጥፎ ተፅዕኖዎች፥ እንቅስቃሴውን የሚፃረሩና የሚፈታተኑ አገር በቀልና የውጭ ኃይላት ተፅኖዎች በርካታ ናቸው።

ይህ 42 ኣመቱን ያስቆጠረው ሕዝባዊ ትግል እነዚህን ሁሉ ተፅኖዎች ታግሎ ልጅነቱን፥ ጎልማሳነቱን፥ አልፎ የሙሉ ሰውነትን ፀጋ ተጎናፅፏል። ከፋም ለማም፥ እንቅስቃሴው ገና ግቡን ባይመታም፥ ቀሪው ጉዞ የዋዛ ባይሆንም፥ በራሱ ግን ፀንቶ እስካሁንም ሳያሰልስ በየምዕራፉ ያሰናከሉትንና አሁንም እያሰናከሉት ያሉትን ፀረ-ህዝብ፤ ፀረ-ዴሞክራሲና ፀረ-ሃገር ኃይላት ተቋቁሞ እዚህ ዕድሜው ላይ መድረሱ በራሱ ታላቅ ድል ነው። በነዚህ የእንቅስቃሴው ዓመታት ውስጥ ለደረሱት በርካታ ጎጂም ሆኑ ጠቃሚ ጉዳዮች ምናልባት እንግዳ ይሆናሉ ተብለው ሊገመቱ የሚችሉት ወታደራዊው ኃይል አብዮቱን ቀልብሶ በአረመኔያዊ ጭፍጨፋው ሕዝብን ከፈጀና ሥልጣኑን ካጠናከረ በኋላና በወያኔው የአገዛዝ ዘመን የተወለዱት ናቸው። እነሱም ቢሆኑ የተሟላና ያልተበረዘ ነው ባይባልም የሰሚ ሰሚ እውቀት ሳያገኙ አይቀሩም ብለን እንገምታለን።

እንዲያም ስለሆነ በዚህ ዕትም በልዩ ልዩ ጊዚያት ተደጋግመው የተነገሩትንና የታወቁትን በርካታ ዝርዝር ጉዳዮች ከማንሳት እንቆጠባለን። ይሁንና ትግሉ በሂደቱ ያስመዘገባቸውን ጎላ ጎላ ያሉ መልካም ውጤቶቹን፥ ያጋጠሙ መሰናከሎችን ብሎም የተከፈለውን ከባድ መስዋትነት ጠቅለል ኣድርጎ ማስቀመጡ ተገቢ ስለሚሆን እንደሚከተለው ሰፍሯል።

- የዛሬ አርባ ሁለት ዓመት የተጀመረው ህዝባዊ ትግል ምንም እንኳን ከህዝቡ 86 እጅ የሆነውን አርሶ አደር በተጨባጭ የመሬቱ ባለቤት ባያደርገውም፥ ለዘመናት ተነፍጎት የቆየውን መብቱን ለማስከበር ባያስችለውም በጥቅሉም ከአዋጅነት አልፎ ፋይዳ ያላመጣለት ቢሆንም፥የፊውዳሉን የመሬት ሥርዓት ግን በጣጦሶ ዳግም እንዳያንሰራራ አድርጎታል። መሬት ለአራሹ ሆኗል የሚለው አዋጅ በጊዜው በአርሶ አደሩና በተቀረው የኢትዮጵያ ሕዝብ ዘንድ የፈጠረው ወደርየለሽ ከፍተኛ የሆነ የደስታ ስሜት ኣንዲህ የዋዛ አልነበረም። ይህ በራሱ የእንቅስቃሴው ዋናውና ጉልህ ውጤቱ ነበር ቢባል ዕውነቱን መናገር ነው የሚሆነው።

- ምንም እንኳን እንደምታው የመሬት ለአራሹን ያህል ነበር ባይባልም፥ የከተማና ትርፍ ቤቶች ፥ በውጭ ዜጎች ይዞታነትና ቁጥጥር ሥር የነበሩ ፋብሪካዎችና የኢንዱስትሪ ልማት ተቋማት በአዋጅ እንዲወረሱ መሆናቸው በወቅቱ በአሠሪው ሲበዘበዝና ሲጨቆን የኖረውን ሠራተኛ ክፍል ስሜት አልነካም ማለት ከቶ የሚቻል አይደለም።

- ለአጭር ጊዜም ቢሆን ማለትም ፋሽስታዊው ወታደራዊ አገዛዝ ኣብዮቱን እስከ ቀለበሰበት 1969 ዓም ድረስ ሕዝቡ በሥርዓተ ለውጡ እንቅስቃሴ ውስጥ በሁሉም መስክ ያሳየው እጅግ የላቀ ተሳትፎ የሕዝብን ታላቅነትና ታሪክ ሠሪነት በተጨባጭ አሳይቷል። በዚህ ወቅት የስነጽሁፍና የኪነት እድገት ከመቅፅበት የተስፋፉበትና ከፍተኛ እመርታ ያስመዘገበበትም ነበር። ማንበብ፥ መወያየት ራስን ማንቃት፥ መደራጀት ማደራጀት የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴ ሆኖ አልፏል። ይህም በራሱ ሌላው የትግሉ ፍሬ ነበር ቢባል ስህተት ኣይሆንም።

- “ንጉሥ አይከሠሥ ሰማይ አይታረስ” እየተባለ የኖረ ሕዝብ በእንቅስቃሴው ያ እንዳልሆነ ሲያይ ባለሥልጣኑና ዋናው ኃይል ራሱና ራሱ ብቻ መሆኑን ሊገነዘብ በቃ። በዚያን ጊዜዋ ኢትዮጵያ እንዲህ ዓይነቱ ግንዛቤ ላይ መድረስ የማይታሰብ ነበርና እንድምታው የትዬ ሌሌ ነበር።

- በዚህ ሕዝባዊ እንቅስቃሴ የተነሱ ሌሎችም ጥያቄዎች ማለትም፥ የሃይማኖትና የፆታ እኩልነት ይረጋገጥ፥ የብሔሮች ጥያቄ በሰላማዊና ዴሞክራሲያዊ መንገድ ይፈታ፥ ሰብዓውና ዴሞክራሲያዊ መብቶች ያለ ገደብ ይከበሩ የሚሉት ጉልህ የሕዝብ ጥያቄዎች ሆነው ተነስተዋል። እንዲሁም ሴቶች ድርብ ጭቆናቸውን ለመታገልና ሠራተኞች ጥቅማቸውንና መብታቸውን የሚያስከብሩበት፥ መምህራን በትምህርት ሥርዓቱ ውስጥ ያላቸው ከፍተኛ ቦታና የራሳቸውንም መብት ለማስከበር ይችሉ ዘንድ ማኅበራቸው ከማናቸውም ሌላ ኃይል ተፅእኖ ነፃ ይሁኑ የሚሉት የማታገያ መፈክሮች ያንጊዜም እንቅስቃሴውን ያሽከረከሩቱም ነበሩ። እነዚህ ሁሉ የያኔው ሕዝብ በእንቅስቃሴው የታገለላቸው ጥያቄዎች ዛሬም መልስ ያላገኙና ትግልን የሚጠይቁ ናቸው።

- የሥልጣን ባለቤቱና ምንጩም ሕዝብ እንደሆነና ይህም ተግባራዊ እንዲሆን ፋሽስታዊው ወታደራዊ አገዛዝ በጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥት እንዲተካ መታገሉ ያን ጊዜ ዋና ነበር። ዛሬም ቢሆን የሕዝቡን የሥልጣን ባለቤትነት ምንጭነት በተጨባጭ ለማረጋገጥ ሁሉን ላሳተፈ ዴሞክራሲያዊ ሕዝባዊ መንግሥት ምስረታ መታገሉ የግድ ነው።

- በኢትዮጵያችን ለሥር ነቀል ለውጥ የተደረገው ትግል በይዘቱም በወርድ በስፋቱም ጠለቅ ያለ ቢሆንም፥ ድንገት ደራሽ ስለነበር ትግሉ ወደፊት እንዲገሰግስና ተግባራዊነቱም ይፋጠን ዘንድ የዚያን ጊዜዋ ኢትዮጵያ ያንን የሚመጥን የዝግጁነት ደረጃ ላይ ነበረች ለማለት ያስቸግራል። ተሸብቦና ታምቆ የኖረ ሕዝብ ነበርና እንዲያው በደፈናው ለፖለቲካው ትግል ፥ ራሱን በፖለቲካ ፓርቲነት ደረጃ በግልፅ

ማደራጀት ቀርቶ፥ የንጉሡን ምሥል አይቶ የሚሰማውን የንዴት ስሜት ደፍሮ ለመናገር የሞከረ መቀመቅ ይወርድበት ከነበረ አገር እንዲህ ዓይነቱ ጉድለት መንፀባረቁ የሚጠበቅና ብዙም የሚያስገርም አይሆንም ቢባል ትክክል ነው። እንዲያውም በዚያች አጭር የእንቅስቃሴ ጊዜ ውስጥ ትግሉ አመራር አግኝቶ ያስመዘገበው ውጤትና፤ በአብዮቱ ተፃራሪዎች እንዳይገታ ያደረገው ታላቅ ተጋድሎ በታሪኩ ውስጥ ደማቅ ሥፍራውን ይዞ ይገኛል።

እነህ በአጭሩም ቢሆን ለማስቀመጥ የሞከርናቸው መልካም ጎኖቹ እንዳሉ ሆነው፥ አሁን ወደ ኋላ መለስ ብለን በዚህ አርባ ሁለተኛ አመቱ ላይ ሆነን ስንቃኝና ስናጤነው ሂደቱ እጅግ ብዙ ውጣ ውረድ፥ መውደቅ መነሳት፥ ወደፊት መገሥገሥ ወደ ኋላ ማፈግፈግ ፥ ጀብደኝነት፥ ዳተኝነት፥ ክህደት አክራሪነት፥ እድርባይነት አምባገነንነት፥ ባንዳነት አንጃኝነት፥ ጠባብነት ትምክህተኝነት፥ ዘረኝነት፥ ጀግንነት ደፋርነት ቆራጥነት አልበገሬነት፥ ፅናት ፍቅር ...ወዘተ የተቀላቀለበት ሕዝባዊ ተውኔት ሆኖ እናገኘዋለን። ይህ በራሱ ውስጥ ይፈጠሩ ከነበሩ ልዩ ልዩ ፈታኝና አስቸጋሪ ሁኔታዎች፥ ሂደቱን ለማጨናገፍ ወይም ለመቀልበስ ከሚታገሉ ኃይሎች ጋር የተደረገ እጅግ እልህ አስጨራሽ ትግል፥ ሕዝባችንንና ታጋዩን ክፍል ከፍተኛ መስዋዕትነት እንዲከፍል አድርጓል።

አነሆ ያች አገሩ በሁሉም መስክ የነበረችበት እጅግ አስከፊ ሁኔታ የቆረቆረው ቀደም ብሎ በተለያዩ ቦታዎችና በተለያዩ ጊዚያት የተደረገ ተቃውሞና አመፅ፥ ኋላም የተማረው ክፍል ሙሉ ጊዜውን ሰጥቶ የተሳተፈበት እንቅስቃሴ ዓላማውና ግቡ የበሰበሰውን የጉልተኛ ሥርዓት ከሥር መሰረቱ ገርሥሶ ጥሎ በምትኩ ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን ዕውን ለማድረግ ነበር። ይሁንና ኢትዮጵያ ያፈራቻቸውን ተኪ የማይገኝላቸውን፥ ብዙ የተማሩ ልጆቿን፥ አፍላቂ ሠራተኞቿን፥ አምራች አርሶ አደሮቿን፥ በወታደራዊ ሳይንስ እውቀታቸውና ተመክሮአቸው አንቱ የተባሉ የጦር መሪዎቿን፥ የአገሪቱን ዳር ድንበር ጠባቂዎች ወታደሮቿን፥ የወደፊት ተስፋዋንና በሁሉም መስክ በእድገት እንድትገሰግሥ ሊያደርጓት ይችሉ የነበሩትን ለጋ ትኩስ ወጣት ልጆቿን ሁሉ ወታደራዊው ፋሽስታዊው ፅልመት በላው። ተስፋዋንና ግሥጋሴዋን ማጨናገፍ ብቻ ሳይሆን፥ ገና ሲጠነሰሱ ጀምረው ዓላማቸውን ኢትዮጵያን ለመበታተን አድርገው በአገሪቱ ሰሜን ክፍል ለተነሱ ኢትዮጵያን በሚጠሉ የውጭ ኃይሎች ለተረዱ ዘረኛና ገንጣይ ኃይሎች አጋልጦ የዛሬ ሃያ አምስት ዓመት ያከተመው የአሥራ ሰባት ዓመቱ ፋሽስታዊ ፅልመት ኢትዮጵያ በታሪኳ ከደረሱባት ዘግናኝ ጊዚያቶች ሁሉ በእንድምታው ከፍተኛውን ቦታ ይይዛል። ወደ ወያኔ ደይን ገፍቶ የወረወረን አረመኔውና ፋሺታዊው ደርግ መሆኑ የሚረሳ አይደለም ። ከዚህ በላይ እንቅስቃሴው በመጀመሪያው ምዕራፉ ውስጥ ያስመዘገበውን መልካም እሴቶቹን ያጋጠሙትን ችግሮችና መሰናከሎቹንና የከፈላቸውን ከባድ መስዋትነት ጠቅለል አድርገን ለማቅረብ ሞከረናል።

የኢትዮጵያ ህዝብ የጀመረውን የሥርዓት ለውጥ እንቅስቃሴ፥ እጅግ የሥልጣን ጥም ያሰከረው መንጋ ፋሽስታዊ ወታደራዊ አገዛዝ ቀልብሶበት ለ17 ዓመታት መላውን አገሪቱን ፅልመት ውስጥ ከቶ ከል አልብሷት ከነበረበት ሁኔታ ውስጥ ወጥቼ፤ በእንቅስቃሴ ውስጥ ያነሳኋቸውን ጥያቄዎቼን የማስመልስበት፤ ብሩህ ተስፋዬ እውን ይሆን ዘንድ ሁኔታዎችን የማመቻችበት፤ በፋሽስታዊው ፅልመት መስዋዕት የሆኑትን ጀግኖች ሁሉ የምዘክርበት፤ ኢትዮጵያ ሰላምንና መረጋጋትን አግኝታ ሁሉም ዜጋዋ በእኩልነትና በአንድነት በፍቅር የሚተሳሰብባት ሊያደርጋት የሚችል ጎሕ ቀዳጅ ሁኔታ ውስጥ ገባሁ ብሎ ተስፋን ሰነቀ። ግን ይህማ ከቶ የሚታሰብ አይሆንም ብለው

ቀድሞውኑም ኢትዮጵያን ሊያፈራርሱና ሕዝቧንም በዘር ፖለቲካ መርዘው ለመከፋፈል ዓላማዬና ግቤ ብለው በተንቀሳቀሱ ኃይሎች ቁጥጥር ሥር መውደቋን የዛሬ ሃያ አምሥት ዓመት ሲረዳ ፥ እጅጉን አዘነ፤ ተቆጣ፤ መጪው ጊዜም የከፋና የሲኦል ሊሆን እንደሚችል አማትሮ ተመለከተ። የተፈራውም አልቀረ ደረሰ። ኢትዮጵያ በታሪኳ ዛሬ የደረሰችበትን ተጨባጭ ሁኔታ በውስጡ እየኖረበት ላለ ሕዝብ እንደ አዲስ ዜና አድርገን እናወሳለታልን ብለን አንዳዳም። የሚያውቀውንና እጅግ ያንገፈገፈውን የወያኔ ህልቆ መሳፍርት የማይገኝለትን በደል ደግመን መደርደሩ ለሕዝባችን ያለንን ፍቅርና አክብሮት ዝቅ ያደርግብናል ብለን ስለምንፈራ፥ ከዚያ ተቆጥበናል። የመልከታችን ትኩረት ግማሽ ምዕተ ዓመት እያስቆጠረ ያለው ለሥር ነቀል የሥርዓት ለውጥ የተደረገ ትግልን መነሻ በማድረግ፥ እጅግ ጠቅለል ባለ መልክ የት ደርሰናል የሚለውን በመዳሰስ ከእንግዲህስ ምን መደረግ ይኖርበታል የሚለውን በግርድፉም ቢሆን ለመጠቆም በመሆኑ ይህንኑ ዘርዝረን መልከታችንን እናጠቃልላለን ።

በኢሕአፓ እምነት፥ በኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ስርአት እንዲሰፍን አገሪቷም የታፈረች የተከበረች አገር እንድትሆን ለማድረግ የተጀመረው ታላቅ ሕዝባዊ እንቅስቃሴ የሕዝብን የሥልጣን ምንጭነትና ባለቤትነት ገና ያላረጋገጠ ቢሆንም፥ በሂደቱ የሚያኮሩና ደማቅ ድሎችን አስመዝግቧል። የተገኘው መልካም ውጤትና የተከፈለው መስዋዕትነት በሚዛን ቢቀመጡ የተከፈለው መስዋዕት ሚዛን የሚደፋ ነው ብለን እናስባለን። ይህም አንድን ኋላ ቀር የሆነ ሥርዓት በሌላ ኣዲስና ተራማጅ ሥርዓት ለመለወጥ የሚደረግ ትግል በእርግጥም የዋዛ እንዳልሆነና የግድ ከባድ መስዋዕት የሚጠይቅ እንደሆነና ለእንግዲሁም እይቀሬ እንደሚሆን በውስጡ አልፈን ዛሬም በትግሉ ፀንተን ቀጥለን ተረድተነዋል። ዛሬ ላይ ሁነን ሕዝባችንና አገራችን የገቡበትን ሁኔታ ስንቃኝ፥ እጅጉን ብናዝንና ልባችን ቢደማም፥ ገና ያልተመለሱ ጥያቄዎች ያሉ ከመሆኑም በላይ በዘር ፖለቲካም እየታመሰች ያለችው አገራችን ህልውናዋ ጭምር እየተናጋ ስለሆነ፥ የአገራችንን አንድነትና ህልውና ለመጠበቅ ኢትዮጵያዊ ዜጋ ሁሉ የድርሻውን እንዲያደርግ ኢትዮጵያ ዛሬም ከምንጊዜውም በላይ ትጠራዋለች ብለን እናምናለን።

ከ3000 ዓመታት በላይ ነፃነቷን ጠብቃ የኖረችው ውድ አገር ኢትዮጵያ፥ ህልውናዋንና ነፃነቷን ጠብቃ እንትቆይ ከልብ በመነጨ የሃገር ፍቅርና ቀናዒነት ሕዝቧ በተደጋጋሚ ደሙን አፍሶላታል፥ አጥንቱን ከስክሶላታል። የኢትዮጵያ ሕዝብ ይህን ያህል የህይወት ዋጋ የከፈለው፥ በመኖሩ ሂደት ውስጥ ሁሉም ነገር ተሟልቶለት፥ ሁሉ በጇ ሁሉ በደጇ ሁኖለት አልነበረም። አብዛኛው አፈር ገፍቶ፥ ጉልበት ሸጦ፥ ጉልት ቸርችሮ ለዘመናት ኑሮውን የገፋ መሆኑም የታወቀ ነው። ይህ የሲኦል ኑሮ ሳያስከፋውና ሳያስቆጣው ቀርቶ ሳይሆን፥ ምሬቱንና ተቃውሞውን ባመፅ ጭምር ሳይገልፅ ቀርቶ ሳይሆን - "ሃገሬ ኢትዮጵያ ሞኝ ነሽ ተላላ የሞተልሽ ቀርቶ የገደለሽ በላ" የሚለውን ብሂልም የተገነዘበ ቢሆንም - ሁልጊዜም ግን ለሃገሩ ካለው ከፍተኛ ፍቅርና ለነፃነቱም ቀናዒ በመሆኑ እንጂ ! አንዳችም ጊዜ በታሪኩ ጉሥቁልናውንና ችግሩን ከአገሩ ህልውናና ነፃነት አስቀድሞም አያውቅም። ይህንን ፅኑ ኢትዮጵያዊነት ስብዕና፥ ከተፈሪም በፊት በተፈሪም፣ ጊዜ በደርግም ጊዜ ጭምር ተጎናፅፎ ቆይቶኣል። ይህን ኢትዮጵያዊነት ስብዕናውን አደብዝዝኔ አጠፋዋለሁ ብሎ ታጥቆ የተነሳውን የወያኔ አገዛዝና ለሆዳቸው ያደሩና በስትራተጂ ግባቸው ከአገዛዙ ጋር የማይጣሉት ኃይሎችም እስካሁን ሲፈታተኑት ቆይተዋል። ይህ በረጅም የታሪክ ጉዞ ሂደት ብዙ ዋጋ የተከፈለበት በርካታ ቀለም ባላቸው ገመዶች ተጋምዶ ያሸበረቀው የኢትዮጵያዊነት አብሮት የሚኖር ባኅርዩን በኋላ ቀሩና በከረፋው የዘረኝነት መጋዝ እየተገዘገዘ ቢሆንም፥ ዛሬም ድረስ እምቢኝ ብሎ እንዳለ አለ። ይህንን ሐቅ ነው የቱንም ያህል ቢመርና ቢጎመራ መቀበል ግድ የሚለው። ይህንን ነው ያ ትውልድ

የወረሰው። ይህንን ነው ያ ትውልድ የወደፊቷ ኢትዮጵያ ተረካቢና ዕጣ ፈንታዋን ለመወሰን ሃላፊነት ላለበት ለዛሬው ኢትዮጵያዊ ወጣት ሁሉ ሊያስተላልፍ የሚሻው።

ኢሕአፓ እነሆ የዛሬ 44 አመት ሲመሠረት ሕዝባችን ያነሳቸው የዴሞክራሲያዊና የሰብዓዊ መብት ጥያቄዎች መልስ እስከሚያገኙ ድረስ ከሕዝቡ ጎን በመሆን እስከመጨረሻው እንደሚታገል ቃል ገብቷል። የኢሕአፓም ትግል አልፋና አሜጋው ይኸው ነው። በመሆኑም፣ ኢሕአፓ ቃል ኪዳኑን እንደገና የማደሱን ገፀ በረከት እያቀረበ፤ የአገሪቱን አንጡራ ሃብት ሙሉ በሙሉ የተቆጣጠረን፥ የጦርና ደህንነት ኃይል በመዳፉ ውስጥ ያስገባን የተደራጀ ኃይል ለማቸነፍና ከሥልጣን ለማስወገድ ብሎም ህዝብን የሥልጣን ምንጭ ያደረገ ሥርዓት በሀገራችን ዕውን ለማረግ፤ በታጋዩ ሕዝብ ዘንድ ከዚያ የላቀ የተዘጋጀ - የተደራጀና የተባበረ፥ ለመስዋዕትነት ቆርጦ የሚነሳ ሕዝባዊ ትግል ወሳኝም ነው ይላል።

ኢሕአፓ ሁልጊዜም በሕዝቡ ውስጥ ከሕዝቡ ጎን ሆኖ መታገሉን ይቀጥላል!!
የኢትዮጵያ ዘረኛና ከፋፋይ የሆነውን የወያኔ አገዛዝ ማስወገዱ አይቀሬ ነው